ነገረ መላእክት

የመጀመሪያ እትም
ሐምሌ 2010

ወልደ ዜና ማርቆስ

Scanned with CamScanner

ማውጫ

1. ቅዱሳን መላእክት....................................1
2. የመላእክት ተፈጥሮ....................................2
3. የመላእክት ቁጥር....................................3
4. ዓለመ መላእክትና አሰፋፈራቸው....................................3
    4.1 በኢዮር ያሉ ነገደ መላእክት....................................4
        4.1.1 አጋእዝት....................................4
        4.1.2 ኪሩቤል....................................4
        4.1.3 ሱራፌል....................................5
        4.1.4 ኃይላት 5
    4.2. በራማ ያሉ ነገደ መላእክት....................................5
        4.2.1 አርባብ....................................5
        4.2.2 መናብርት....................................5
        4.2.3 ስልጣናት....................................6
    4.3. በኤረር ያሉ ነገደ መላእክት....................................6
        4.3.1 መኳንንት....................................6
        4.3.2 ሊቃናት....................................6
        4.3.3 መላእክት....................................6
5. የመላእክት ባሕርይ 7
6. የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት....................................7
    6.1. የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት በብሉይ ኪዳን......8
    6.2. የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት በሐዲስ ኪዳን......9
7. የቅዳሳን መላእክት አዳኝነት እና አማላጅነት....................................10
    7.1 የቅዱሳን መላእክት አዳኝነት....................................10
    7.1 የቅዱሳን መላእክት አማላጅነት....................................12
    7.3 የቅዱሳን መላእክት ጠባቂነት 13
8. ቅዱሳን መላእክት ስግደትና ክብር ይገባቸዋል 13
9. መልአኩ ቅዱስ ዮሐንስን ለምን አትስገድልኝ አለው....................................14
    9.1 ስለትህትና 14
    9.2 ስለቅዱስ ዮሐንስ ክብር 14
    9.3 ስለ ሥልጣነ ክህነት ክብር....................................15
10. ድርሳነ ቅዱስ ገብርኤል ዘሐምሌ....................................15
11. ማጠቃለያ....................................18

Scanned with CamScanner

1. ቅዱሳን መላእክት

መላእክት ማለት

1ኛ. አለቃ ሹም አበጋዝ ተሸሞ ከንጉስ የተላከ ማለት እንደሆነ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በመጽሐፈ ሰዋስው ወግስ መጽሀፋቸው ገለጠውታል። ነው ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ‹‹ለምንት አንገለጉ አሕዛብ ወሕዝብኒ ነበቡ ከንቶ ወተነሥኡ ነገስተ ምድር ወመላእክትኒ ምስሌሆሙ ኅቡረ›› አሐዛብ ለምን ያጉረመርማሉ ወገኖችስ ለምን ከንቱን ይናገራሉ የምድር ነገሥታት ተነሡ አለቆችም በእግዚአበሔርና በመሲሑ ላይ ተማከሩ። መዝ 2፥2-3 የተሠመረበት ቃል በግዕዝ መላእክት የሚለው ቃል በአማርኛው አለቆች ተብሎ ተተርጉሟል። እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቆላስይስ መልእክቱ እንደተናገረው ‹‹ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ እየወደደ ባላየውም ያለ ፈቃድ እየገባ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ ማንም አይፍረድባችሁ። ቆላ 2፥18 □እዚህ ላይ የመላእክትን አምልኮ ሲል የአለቆችን የሹማምንትን የውሸት ትህትናና አምልኮ ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው። እንዲሁም በራእየ ዮሐንስ የተገለጡት ሰባቱ የቤተ ክርስቲያን አለቆች መላእክት ተብለው ተጠርተዋል።

2ኛ. የእግዚአበሔር መልእክተኞች ለማያውያን ረቂቃን ማለት ነው ዕብ 1፥14 ይኸውም የመላእክትን ተግባር የሚያሳይ ነው የእግዚአብሔርን ቸርነትና ምሕረት ወደ ሰው የሰውንም ጸሎትና ልመና ወደ እግዚአብሔር ለማድረስ ይላካሉና ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር 90፥12 መላእክቱን ስለአንተ ያዝዛቸዋል እንዳለ መልእክተኞች ማለት ነው። ተፈጥሮአቸው የተቀደሰ ሕይወታቸውም በቅድስና የተመላ በመሆኑ ቅዱሳን ይባላሉ።በመንፈሳዊ ዓለም እየኖሩ በሰማይም በምድርም እግዚአብሔርንና ሰውን ያገለግላሉ።በዚህ ተግባራቸው ከእግዚአብሔርና ከቅዱሳን ሰዎች ጋር አንድነት አላቸው። ከተፈጠሩበት ዕለትና ሰዓት ጀምሮ ከቅዳሴና ከማኅሌት ከአገልግሎት ተለይተው አያውቁም ዕረፍታቸው ምስጋናቸው፣ምስጋናቸውም ዕረፍታቸው ነው።ኢሳ 6፥3፣ራዕ 4፥8።ቅዱሳን መላእክት በጥቅል ስማቸው የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉ ኢዮ 1፥6፤ መናፍስት ተብለው ይጠራሉ ዕብ 1፥14፤ ጠባቂዎች ተብለው ይጠራሉ ዳን 4፥7፣ ማቴ 18፥10፤ ቅዱሳን ተብለው ይጠራሉ ዘካ 14፣3፣ ማቴ 25፥31።

Scanned with CamScanner

በስም ተለይተው ከሚታወቁት የቅዱሳን መላእክት ነገዶች መካከል ጥቂቶቹ ነገደ መላእክት፣ አጋዕዝት፣ ሥልጣናት፣ ኃይላት፣ መናብርት፣ መኳንንት፣ ሊቃናት፣ አርባብ፣ ኪሩቤል፣ ነገደ ሱራፌል ይገኙበታል። እነዚህም ነገዶች የእያንዳዳቸው የነገድ አለቆች ያሏቸው ሲሆን በስም ከሚታወቁት ጥቂቶቹ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ሩፋኤል፣ ፋኑኤል፣ ራጉኤል፣ ኡራኤል፣ ሳቁኤል፣ አፍኒን ተጠቃሾች ናቸው።

2. የመላእክት ተፈጥሮ

ሕያው እግዚአብሔር በዕለተ እሑድ ከፈጠራቸው ፍጥረታት መካከል ቅዱሳን መላእክት ይገኛሉ። ኩፋ.2፡7-8 መዝሙረኛው ክቡር ዳዊትም ይኽን በማስመልከት፡- "በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ተፈጠሩ፤ የሰማይ ሠራዊትም ኹሉ በአፉ እስትንፋስ" ይላል /መዝ.32፡6/።

ምንም እንኳን በመዠመሪያው ቀን የተፈጠሩ ቢኾኑም ግን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋና ከሰባቱ ሰማያት በኋላ በ9ኛው ሰዓተ ሌሊት ነው የተፈጠሩት። ይኽ ለምን እንደኾነ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ አክሲማሮስ በተባለ መጽሐፉ ላይ፡- "በፊት ፈጥሯቸው ቢኾን እኛም አብረነው ፈጠርን፤ ያዠንለት፤ ተራዳነው ባሉ ነበር። አንድም ርሱ ቢመሠርት እኛ ገነባን፤ ርሱ ቢገነባ እኛ መሠረትን ባሉ ነበር። ይኸም ሳጥናኤል በኋላ እኔ ፈጠርኲችኍ እንዳለው ማለት ነው" በማለት ያብራራል /አክሲማሮስ ዘእሑድ፣ ገጽ 24/።

ቅዱሳን መላእክት ተፈጥሮአቸው ኢመዋትያን /የማይሞቱ/ ናቸው። ዘንተ ዓለም በቅድስና ቆመው እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ይኖራሉ።

ቅዱሳን መላእክት ፈጻምያነ ፈቃድ ናቸው የእግዚአብሔርንና የሰውን ፈቃድ ሲፈጽሙ ይኖራሉ።

ቅዱሳን መላእክት (አልቦ ፍፃሜ ለመዋዕሊሆሙ) ለዘመናቸው ፍፃሜ አይነገርላቸውም።ቅዱሳን መላእክት ተፈጥሮአቸው ከምንም ካለ መኖር ወደ መኖር ነው ዳዊት በመዝሙሩ መላእክቱን መንፈስ (ነፋስ) አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ መዝ 103፥4።በማለት የተናገረው።

- እንደ እሳትና ነፋስ ረቂቅ መሆናቸውን
- ለተልዕኮ የሚፋጠኑ መሆናቸውን

Scanned with CamScanner

➢ ኃያልነታቸውን፣ፈጻምያነ ፈቃድ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው እንጂ ከእሳትና ከነፋስ ተፈጥረዋል ለማለት አይደለም፡፡

ድርሳነ ሚካኤል ውስጥ "ሰላም ለገጽከ እምነፍስ ወነድ ዘተሠዐለ ምስለ ማይ ወመሬት ዘኢተሀወለ" የሚል ገጽ ንባብ ቢገኝም ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ከተናገረው ጋር ተመሳሳይ ነው እንጂ ተፈጥሮአቸው ከእሳትና ከነፋስ ማለት አይደለም፡፡

መላእክት ከእሳትና ከነፋስ ተፈጥረዋል ከተባለ ኃላፍያን፣ጠፊዎችና መሬታውያን ናቸው ማለት ይሆናል፡፡እሳትና ነፍስ ያልፋሉና "ሶበሰ ተፈጥሩ እምነፋስ ወእሳት እሞቱ ወእማሰኑ ከማነ ከእሳትና ከነፋስ ተፈጥረውስ ቢሆን ኖሮ እንደ እኛ በሞቱ ነበር" በማለት አክሲማሮስ ተናግሮአል፡፡

3. የመላእክት ቁጥር

ቅዱሳን መላእክት አንድ ጊዜ የተፈጠሩ በየጊዜው የማይባዙ የማይሞቱ እና ቁጥራቸውም ብዙ የብዙ ብዙ ነው ይህም በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መላእክት ቁጥር የተጻፉትን ስንመለከት፡-

➢ ‹‹ዙፋኖችም እስኪዘረጉ ድረስ አየሁ በዘመናት የሸመገለውም ተቀመጠ፡፡...ሺህ ጊዜ ሺህ ያገለግሉትም ነበር፡፡ እልፍ አእላፋትም በፊቱ ቆመው ነበር፡፡›› ዳን 7፡10

➢ ‹‹ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ፡፡›› ሉቃ 2፡20

➢ ‹‹አየሁም በዙፋኑም በእንስሶቹም በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ ቍጥራቸውም አእላፋት ጊዜ አእላፋትና ሺህ ጊዜም ሺህ ነበር፡፡›› ራእ.ዮሐ 5፡11

4. ዓለመ መላእክትና አሰፋፈራቸው

የቅዱሳን መላእክት አሠፋፈርን በተመለከተ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ አክሲማሮስ በተባለ መጽሐፉ እግዚአብሔር መላእክትን በዕለተ እሁድ ፈጥሮ በኢዮር፣በራማ፣በኤረር በከተማ አሥር በነገድ ደግሞ መቶ አድርጎ እንደአሠፈራቸው ተናግሯል፡፡

ቅዱሳን መላእክት በነገድ መቶ መሆናቸውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሮአል፡፡ማቴ 18፥12፡፡ከመቶው አንዱ ዲያብሎስ ነበር በዲያብሎስ ፈንታም አዳም ተተክቷል "የጠፋውና የተፈለገው" አዳም ነው፡፡ በከተማ አሥር ስለ መሆናቸውም ዐሥር ድሪም ያላት ብትኖር አንዲቱ ብትጠፋባት

Scanned with CamScanner

መብራት አብርታ በቤቷ ያለውን ሁሉ እየፈነቀለች እስክታገኛት ድረስ ተግታ ትፈልግ የለምን በማለት አስረድቷል፡፡ሉቃ 15፥8 ከሰባቱ ሰማያት መካከል ሦስቱ ሰማያት ማለትም ዓለመ መላእክት የመላእክት ከተማ /መኖሪያ/ ሲሆኑ እግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክትን በነገድ መቶ በከተማ አሥር አድርጎ በሦስቱ ሰማያት በኢዮር፣ በራማና በኤረር አስፍሯቸዋል፡፡

4.1 በኢዮር ያሉ ነገደ መላእክት

ኢዮር ከሰባቱ ሰማያት ውስጥ በአምስተኛ ደረጃ ላይ ስትገኝ እግዚአብሔር በዚህች ከተማ ላይ ዐርባውን ነገደ መላእክት አስፍሯቸዋል፡፡ ሲያስፍራቸው ለዐራት ክፍሎ ዐራት ዐለቆችን ሾሞላቸዋል፡፡ እነዚህንም ሲፈጥራቸው በ10 ኛው ሰዓት ሌሊት ኢዮርን እንደፎቅ ላይ ቤት፣ ታች ቤት፣ ምድር ቤት አድርጎ ፈጥሯቸዋል፡፡

4.1.1 አጋእዝት

የመጀመሪያዎቹን በኢዮር ያሰፈራቸውን የመላእክት ነገዶች አጋእዝት ብሎ ጠራቸው፡፡ አለቃቸውን ሳጥናኤልን አድርጎ ሾመላቸዋል፡፡ሣጥናኤል ማለት ቅሩብ እግዚአብሔር አጋዜ መንጦላእት፣ አቅራቤ ስብሐት ማለት ነው፡፡ በኋላም ሣጥናኤል አምላክነትን ሽቶ ከክብር በመውረዱ ቅዱስ ሚካኤል ተረክቦታል፡፡

4.1.2 ኪሩቤል

በሁለተኛው ከተማም ዐሥሩን ነገደ ኪሩቤል ብሎ ከሰየማቸው በኋላ ኪሩብ የተባለውን መልአክ አለቃ አድርጎ ሾመላቸው፡፡ እነዚህም የቀሳውስት አምሳል ናቸው፡፡ ሕዝ 1÷6-7

ሕዝ 10÷1 ‹‹እኔም አየሁ፣ እነሆም በኪሩቤል ራስ ላይ ባለው ጠፈር በላይቸው እንደ ሰንፔር ድንጋይ ያለ እንደዙፋን የሚመስል መልክ ተገለጠ ›› እንዲል፡፡

እነዚህንም ከወገባቸው በታች አንድ ከወገባቸው በላይ አራት አድርጎ ፈጥሯቸዋል፡፡ እነዚህም 4 ገፅ ይባላሉ፡፡ ገፀ ሰብእ፣ ገፀ አንበሳ፣ ገፀ ንስር፣ ገፀ እንስሳ (ላም) ይባላሉ፡፡ ከእግራቸው እስከ ራሳቸው በዓይን የተሸለሙ ናቸው፡፡ እነዚህ ኪሩቤል እንደነብር ዡንጉርጉር አንድም እንደመስታወት ብሩህ ናቸው፡፡

Scanned with CamScanner

4.1.3 ሱራፌል

በሦስተኛው ከተማም ዐሥሩን ነገደ ሱራፌል ብሎ ሰየማቸው፡፡ እነዚህም የዲያቆናት አምሳያ ናቸው፡፡ አፈጣጠራቸውም ስድስት ክንፍ አድርጐ ፈጥሯቸዋል፡፡ ኢሣ 6÷2 ‹‹ሱራፌል ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር ለእያንዳንዱም ስድስት ክንፍ ነበረው በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር በሁለቱም ክንፍ እግሮቹን ይሸፍን ነበር፡፡ በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር›› እንዲል የእነኚህም አለቃቸው ገፀ ንስር፣ ገፀ እንስሳ ነው ስሙም ሱራፌ መልአክ ይባላል፡፡

4.1.4 ኃይላት

በዐራተኛው ከተማም ዐሥሩን ነገድ ስማቸውን ኃይላት አላቸው እነዚህ የሥላሤ ሰይፍ ጃግሮች፣ ሰይፉ ያገሮች ናቸው የኃይላት አለቃቸው ቅዱስ ሚካኤል ሲሆን እነዚህንም ከነአለቃቸው በኢዮር በዐራተኛው ሰማይ አስፍሯቸዋል፡፡ ሄኖክ 10፡2-6 1ጴጥ 3÷22፡፡እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሁኜ አሁን መጥቻለሁ፡፡ኢያ 5÷14 ከአለቃችሁ ከሚካኤል በቀር ማንም የሚያጸናኝ የለም፡፡ዳን 10÷21 ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል፡፡ ዳን 12÷10 የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ይሁዳ ቁ.9 እንዲል፡፡

4.2. በራማ ያሉ ነገደ መላእክት

እግዚአብሔር በ10ኛው ሰዓት ከሰባቱ ሰማያት በስድስተኛዋ ሰማይ በራማ ያሉትን መላእክት በ3 አለቃ አድርጐ ለሦስት ክፍሎ አሰፈራቸው፡፡ ሲያሰፈራቸውም ራማን እንደ ላይና ታች ቤት፣ እንደምድር ቤት አድርጐ በ3 ከተማ አስፍሯቸዋል፡፡ እነዚህም

4.2.1 አርባብ

የመጀመሪያዎቹን የራማ የላይኞቹን አሥሩን የመላእክት ነገዶች አርቦብ ብሎ ሰየማቸው፡፡ እነዚህም በእግዚአብሔር ፊት ቋሚዎች አጋፋሪዎች ናቸው፡፡ ሄኖክ 10፡7-8 ‹‹እኔ እግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ ›› ሉቃ 1÷19 እንዲል የአርባብ አለቃቸው ቅዱስ ገብርኤል ነው፡፡

4.2.2 መናብርት

በራማ ያሉትን ሁለተኛዎቹን ዐሥሩን ነገድ ስማቸውን መናብርት አላቸው፡፡ አለቃቸውም ቅዱስ ሩፋኤል ነው፡፡እነዚህም የሥላሴ ጋሻ ጃግሮች ናቸው፡፡ የመብረቅ ጋሻ፣ የእሳት ጦር ይዘው ለዘለዓለም እንደነፋስ ሲበሩ ይኖራሉ፡፡ እነዚህንም በራማ ሁለተኛው ከተማ ላይ አስፍሯቸዋል፡፡ሄኖክ 10፡6-7

Scanned with CamScanner

4.2.3 ስልጣናት

እግዚአብሔር በራማ ያሉትን ሦስተኛዎቹን ዐሥሩን ነገድ ስማቸውን ስልጣናት አላቸው:: አለቃቸው ሱርያል መልአክ (ቅዱስ ዑራኤል) ነው:: እነዚህም የሥላሴ ነጋሪት መቺዎች፣ መለከት ነፊዎች ናቸው:: መላእክትን ለቅዳሴ፣ ለስባሔ ሲያነቁ፣ ሲያተጉ የሚኖሩ ናቸው:: እነዚህንም በራማ በሦስተኛው ከተማ አስፍሯቸዋል:: 1ኛ ጴጥ 3÷22

4.3. በኤረር ያሉ ነገደ መላእክት

እግዚአብሔር አምላክ በ11ኛው ሰዓት ሌሊት በሰባተኛዋ ሰማይ በኤረር ያሉትን መላእክት በ3 አለቃ በ30 ነገድ አድርጐ ኤረርን እንደ ላይ ቤት፣ ታች ቤት፣ ምድርቤት አድርጎ ከፍሎ አስፍሯቸዋል:: እነዚህም

4.3.1 መኳንንት

የመጀመሪያዎቹን በኤረር ያሉትን ዐሥሩን ነገደ መላእክት መኳንንት ብሎ ከሰየማቸው በኋላ አለቃቸውን ሰዳክያል መልአክ አድርጐ ሾመላቸው:: እነዚህም የሥላሴ ቀስተኞች ናቸው:: ተራራ የሚንድ ድንጋይ የሚሰነጥቅ የእሳት ፍላፃ የእሳት ቀስት ይዘው ሰውን ሁሉ ከመከራ ሥጋና ከመከራ ነፍስ የሚጠብቁ ናቸው:: በተጨማሪም በትንሣኤ ዘጉባኤ የሰውን ሁሉ አጥንት የሚሰበስቡና ምድርን ለምጽአት እንዲያዘጋጁ የሚላኩ ናቸው::ማቴ 24:31-32

4.3.2 ሊቃናት

በኤረር ያሉትን ሁለተኛዎቹን ዐሥሩን ነገደ መላእክት ስማቸውን ሊቃናት አላቸው:: አለቃቸውም ሰላትያል መልአክ አድርጐ ሾመላቸው:: እነዚህም የሥላሴ የፈረስ ባልደራስ ናቸው:: በእሳት ፈረስ ተቀምጠው የእሳት ልብድ ተለብደው፣ በከዋክብት አምሳል የብርሃን ሰላጢን ይዘው በልባቸው የሚሳቡ፣ በእግራቸው የሚሽከረከሩትን፣ በክንፋቸው የሚበሩትን በደመ ነፍስ ሕያዋን የሆኑትን ሁሉ የሚጠብቁ ናቸው::

4.3.3 መላእክት

እግዚአብሔር አምላክ በኤረር ያሉትን በሦስተኛ ከተማ አድርጐ ዐሥሩን ነገድ መላእክት ብሎ አስፍሯቸዋል:: አለቃቸውም አናንኤል መልአክ አድርጐ ሾመላቸው:: እነዚህ እንደ ብረት የጸና የእሳት ነጐድጓድን ወደምድር

የሚወነጭፉ፣ የፀሐይን፣ የጨረቃን፣ ከዋክብትን፣ አዝርዕትን፣ አትክልትን፣ እፅዋትን ከምድር በላይ ከሰማይ በታች የተፈጠሩትን ሁሉ የሚጠብቁ ናቸው። ኩፋሌ 2÷6-8 በ3ቱ ሰማያት ያሉት አስር አለቆችና መቶ ነገድ እነዚህ ናቸው። ሄኖክ 20÷38-42

5. የመላእክት ባሕርይ

መላእክት በፍጥረታቸው ረቂቃን መናፍስት ስለሆኑ ሥጋና አጥንት የላቸውም። ማዕረገ ርቀትንም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ሲያስረዱ ከሰው አካል የሰው ሐሳብ ይረቃል ከሰው ሐሳብ የሰው ነፍስ ትረቃለች፤ ከሰው ነፍስ የመላእክት አካል ይረቃል ከመላእክት አካል የመላእክት ሐሳብ ይረቃል፤ ከመላእክት ሐሳብ ደግሞ ሥላሴ ይረቃሉ። መዝ 104፡3 እንደ ሰው አይራቡም፤ አይጠሙም ልብስ፣ መጠለያ አይፈልጉም። "እኔም ተገለጥኩላችኁ፤ ነገር ግን እይታን አያችኁ እንጂ ከእናንተ ጋር አልበላኹም፤ አልጠጣኹምም" ጦቢ.ት 12፡19 እንዳለ የመላእክት ምግባቸው የእግዚአብሔር ምስጋና መጠጣቸውም የመለኮት ፍቅር ነው።

6. የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት

የቅዱሳን መላእክት ቀዳሚው አገልግሎታቸው የፈጠራቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ማመስገን ነው። ሲያመሰግኑም "የመናፍስት ጌታ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ነህ፤ ፍጥረትህም ምድርን ይሞላል እያሉ ያከብራሉ፤ ያመስግናሉ፤ ከፍ ከፍም ያደርጋሉ" ኄኖክ 9÷39፣ ኢሳ 6÷2-4። እንዲሁም በዮሐ ራዕ 4÷11 እንደምናነበው "ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና በፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብርና ውዳሴ ኃይል ላንተ ይገባል" እያሉ የአማልእክት አምላክ፣ የጌቶች ጌታ፣ የንጉሦችም ንጉሥ እግዚአብሔር አምላካችንን ያመሰግናሉ።

በሌላም ሥፍራ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ "አየሁም በዙፋኑ በእንስሶች በአለቆች ዙሪያ የብዙ መላእክት ድምጽ ሰማሁ ቁጥራቸውም የብዙ ብዙ እልፍ አእላፋት ነበር በታላቅ ድምጽ እንዲህ አሉ ለታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት ጥበብና ብርታትንም ክብርና ምስጋናንም በረከትንም ሊቀበል ይገበዋል። በሰማይና በምድር ከምድርም በታች በባህርም ላይ ያለው ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለው ሁሉ በረከትና ክብር ምስጋናና ኃይልም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በዙፋኑ ለተቀመጠው ለበጉ ይሁን ሲሉ ሰማሁ" ራዕ 5÷11-14።

Scanned with CamScanner

ቅዱሳን መላእክት ከምስጋና አገልግሎታቸው ቀጥሎ ለፍጥረት የፈጣሪያቸው የኃይሉ፣ የቸርነቱ የምህረቱ መገለጫዎች ናቸው። ይህ አገልግሎታቸው በተለይም በአዳምና በልጆቹ ጎልቶ ይታያል።ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረ ጊዜ ደስታቸው ወደር አልነበረውም ኢዮብ እንደተናገረው ‹‹የእግዚአብሔር ልጆች እልል ይሉ ነበር›› ኢዮ 38፡6 ምክንያቱም ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ስለሆነ ፈጣሪያቸውን ስለሚመስል የሰውን ልጅ አብዝተው ይወዱታል።

6.1. የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት በብሉይ ኪዳን

አባታችን አዳም በፈጸመው ስሕተት ከገነት በተሰደደ ጊዜ በንስሐ ሆኖ በተስፋ እንዲጽናና ቅዱሳን መላእክት ይረዱት ነበር። ሄኖክም ስለቅዱሳን መላእክት አገልግሎት "በዚያም ዐይኖቼ ከመላእክት ጋር ማደሪያቸውን፣ ከቅዱሳንም ጋር ማረፊያቸውን አዩ። ስለሰው ልጆች ይለምናሉ፣ ይማልዳሉ፣ ይጸልያሉም" ሄኖክ 9፥22-23 ሲል ተናግሯል። አባታችን ኖኅም ዓለም ለድምሳሴ በቀረበ ጊዜ በመርከብ ሥራው ይረዱት የነበሩት ቅዱሳን መላእክት ናቸው። አበ ብዙኃን የተባለው አባታችን አብርሃም ከካራን በወጣ ጊዜ ጀምሮ የመላእክት ጥበቃ አልተለየውም፤ በመሆኑም "ኢያቦር" የተባለ አገልጋዩን ወደ ሶርያ ወደ ባቱኤል ቤት በላከው ጊዜ "የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር፥ እርሱ መልአኩን በፊትህ ይሰድዳል" በማለት ልኮታል ዘፍ 24፥7።

አባታችን ያዕቆብም "ከሕፃንነቴ ጀምሮ እስከዚች ቀን ድረስ ያሳደገኝ የመገበኝ እግዚአብሔር መልአኩን ሰዶ ከመከራውም ሁሉ ያዳነኝ እሱ እነዚህን ሕፃናት ያክብራቸው" በማለት እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ እንዳዳነው፣ እንደጠበቀው ያስረዳል ዘፍ 48፥16።

እስራኤልንም በመልአኩ መሪነት ወደ ምድረ ርስት መጓዛቸው ለሙሴ ተገልጾለታል "በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ ወደ አዘጋጀሁልህ ሥፍራ ያገባህ ዘንድ እነሆ እኔ መልአኬን በፊትህ እልካለሁ ራስህን ጠብቅ ስማውም እምቢም አትበለው ስሜ በእርሱ ስለሆነ ይቅር አይልም" ዘጸ 23፥20-21። እሥራኤል ዘሥጋ ምድረ ከነአንን ይወርስ ዘንድ ከግብፅ በወጣ ጊዜ መንገድ የሚመራውንና ምድሪቱን እስከሚወርስ ድረስ የሚጠብቀው መልአክ እንደታዘዘለት ሁሉ እሥራኤል ዘነፍስ የሆን እኛ ክርስቲያኖችም አሁንም መንገድ በተባለው ዕድሜአችንና ርስት የተባለችውን መንግስተ ሰማያት እስከምንወርስ እስከ እለተ ምጽአት ድረስ የመላእክት ጥበቃ አይለየንም።

Scanned with CamScanner

ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ "እስመ ለመላእክቲሁ ይኤዝዞሙ በእንቲአከ ከመ ይዕቀቡከ በኵሉ ፍናዊከ ወበእደዊሆሙ ያነሥኡከ ከመ ኢትትዐቀፍ በዕብን እግርከ" — "በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለእናንተ ያዛቸዋል እግርህንም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሱሃል" መዝ 90 ፥11-12:: መንገድ በተባለ በዚህ ዓለም የኑሮ ዘመናችን ሁሉ ይጠብቁን ዘንድ እግራችን በድንጋይ እንዳይሰናከል ማለት እግረ ኅሊናችን በኃጢአት፣ በዲያብሎስ ወጥመዶች እንዳንያዝ ይረዱናል:: "ከቶ ለማን ብሎአል ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?" እንዳለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ:: ዕብ 1፥14::

ቅዱሳን መላእክት በእያንዳንዱ የኑሮ ተግዳሮቶች ሁሉ ጣልቃ ገብተው ይታደጉናል:: ሎጥን ከጥፋት ከተማ፣ ያዕቆብን ከላባና ከኤሳው ቁጣ፣ ዳንኤልን ከአንበሶች አፍ፣ ሠለሥቱ ደቂቅን ክእቶን እሳት ታድገዋል:: ዘፍ 19፥1-22፣ ዘፍ 32፥1:: የተራቡትን መግበዋል፤ ነቢዩ ኤልያስ ከኤልዛቤል ሸሽቶ በምድረ በዳ በረኃብ ደክሞ በተኛበት መልአኩ ምግቡን በአገልግል ወኃውን በመንቀል አቅርቦ መግቦታል 1ኛ ነገ 19፥5-7:: ዳንኤልንም በቂሮስ ንጉስ ፋርስ ስድስት ቀን ሙሉ በአንበሳ ጉድጓድ በተጣለበት ጊዜ መልአኩ ዕንባቆምን በአንበሶች ጉድጓድ በባቢሎን ላለ ለዳንኤል ይህንን የያዝከውን ምግብ ውሰድለት ብሎት ከይሁዳ እስከ ባቢሎን መልአኩን ወስዶ አስመግቦ መልሶታል ዳን 14፥32-38::
የእግዚአብሔር መልአክ ሊያጠቁን ከሚመጡ የሥጋ ጠላቶችም ይታደጉናል፤ በዙሪያችንም አጥር ቅጥር ሆነው ይጠብቁናል "የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሠፍራል ያድናቸውማል" መዝ 33፥7፣ 2ኛ ነገ 6፥16-18::

6.2. የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት በሐዲስ ኪዳን

በሐዲስ ኪዳን መባቻ ላይ መላእክት የነበራቸው አገልግሎት የምሥራች ነበር:: ለካህኑ ዘካርያስ ልደተ ዮሐንስን መልአኩ በምሥራች ነገረው ሉቃ 1፥11-17:: ይኸው መልአክ ሥጋዊ ወልደ እግዚአብሔርን እንበለ ዘርአ ብእሲ ለምትወልደው ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም በምስጋና አበሠራት:: ሉቃ 1፥26-38:: የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በቤተልሔም መወለድ ተግተው መንጋቸውን ይጠብቁ ለነበሩ እረኞች ቅዱሳን መላእክት አበሠሩ:: በጌታ ልደት ሰውና መላእክት "ስብሐት

ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ" እያሉ በአንደነት ዘመሩ:: ሉቃ 2፥8-20::

በጌታችን ትንሣኤም የምሥራቹ በመላእክት ታወጀ:: "ሕያውን ከሙታን መካከል ለምን ትፈልጋላችሁ እነሆ ተነስቷል" በማለት ሉቃ 24፥5:: በጌታችን ዕርገትም "እናንት የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እያያችሁ ለምን ቆማችኋል ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ ያረገው ኢየሱስ እንዲሁ ዳግመኛ ይመጣል" የሐ ሥራ 1፥11:: "ለምን ቆማችኋል" በማለት የጊዜን ጥቅምና ወንጌልን ነገረ ምጽአቱን ለዓለም ሁሉ ይሰብኩ ዘንድ መክረዋቸዋል::

በስብከተ ወንጌልም መላእክት ተገቢውን ሥራ አከናውነዋል:: አሁንም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እያከናወኑ ይገኛሉ:: በቤተክርስቲያን መስፋት የቀኑ ካህናተ አይሁድና ሰዱቃውያን ሐዋርያትን በወህኒ አሳስረዋቸው የእግዚአብሔር መልአክ በሌሊት የግዞቱን ቤት ደጃፍ ከፍቶ አወጣቸው እንዲህም አላቸው "ሒዱ ወደ ምኩራብም ግቡ፤ ለሕዝብም ይህንን የሕይወት ትምሕርት አስተምሯቸው" የሐዋ ሥራ 5፥19-20:: ሄሮድስ አይሁድን ለማስደሰት ቅዱስ ጴጥሮስን ካሰረበት ወህኒ ቤት የእግዚአብሔር መልአክ (ቅዱስ ጴጥሮስን) ከእስር ፈትቶ አውጥቶታል:: የሐዋ ሥራ 12፥ 6-19::

ቅዱሳን መላእክት ሃይማኖት የጎደላቸውን ሰዎች ከአህዛብ ቤት ሳይቀር እንደነ ቆርኔሌዎስ ያሉትን ከሐዋርያት ጋር በማገናኘት እንዲጠበቁና ወንጌልን እንዲሰሙ ረድተዋል:: የሐዋ ሥራ 10፥1-7::

7. የቅዱሳን መላእክት አዳኝነት፣አማላጅነት እና ጠባቂነት

በአጠቃላይ ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ለአገልግሎት የሚፋጠኑ ናቸው:: ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትና ቸርነት እውቀትና ጥበብ ይዘው ወደ ሰው ይመጣሉ::ዳን 9፥22::

የሰዎችን ጸሎትና ልመና ወደ እግዚአብሔር ያሳርጋሉ ሐዋ 9፥1::

ቅዱሳን መላእክት በአርአያ እግዚአበሔር እና በአምሳለ እግዚአብሔር የተፈጠርነውን የሰውን ልጆች፡ ከመከራ ሲያድኑ ፤ከፈጣሪው ሲያማልዱ እና ከክፉ ነገር ሁሉ ሲጠብቀቁ ይኖራሉ::

7.1 የቅዱሳን መላእክት አዳኝነት

የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሠፍራል ያድናቸውማል::መዝ 33፥7:: እዚህ ላይ መመልከት የሚገባን ነገር ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ቅዱሳን መላእክትን ሲገልጥ

1ኛ. የእግዚአብሔር መልአክ ማለቱን ነው ቅዱስ ዳዊት ይህን ያለበት ምክንያት የእግዚአብሔር ያልሆነ ፍጥረት ኖሮ አይደለም እንደውም በ23 ኛው መዝሙሩ ‹‹ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ ዓለምኒ ወኩሎሙ እለ የኀብሩ ውስቴታ›› መድርና መላዋ የእግዚአብሔር ነው በማለት የሁሉ ፈጣሪ የሁሉ አስገኝ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደሆነ ነግሮናል። መዝ 23፡1 ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስም ‹‹ወቦቱ ኩሉ ኮነ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ›› ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች እንኳን ያለእርሱ አልሆነም በማለት ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔር ገንዘብ እንደሆነ ያረጋግጣል። ዮሐ 1፡3 ጣዲያ ክቡር ዳዊት ቅዱሳን መላእክትን የእግዚአብሔር መላእክት በሎ የጠራቸው ከርኩሳን አጋንንት ተለይተው እግዚአብሔርን በማመስገን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ጸንተው መኖራቸውን ለመግለጥ ነው። ስለዚህ እኛ የምናከብራቸው የምንስገድላቸው የምንማፀናቸውና በቃል ኪዳናቸው የመንታመንባቸው መላእክት የእግዚአብሔር ስለሆኑ እንጂ መላእክት በመሆናቸው ብቻ አይደለም። ርኩሳን መላእክትም በተፈጥሮአቸው መላእክት ቢሆኑም ከእግዚአብሔር ስለተለዩ እግዚአብሔርንም ስለማያመሰግኑ እኛም አንወዳቸውም ይልቁንም እንረግማቸዋለን እንጂ። በጸሎታችንም መጀመሪያ ላይ ‹‹በቅድስት ሥላሴ እያመንኩ እና እየተማፀንኩ ጠላቴ ሰየጣንን እክድሃለሁ በዚህች በእናቴ ቤተክርስቲያን ፊት ቆሜ እክድሃልሁ ለዚህም ምስክሬ ማርያም ናት›› በማለት ዲያበሎስንና ሠራዊቱን እንደመንጠላቸውና እንደምንረግማቸው እናረጋግጣለን።

2ኛ. <u>በሚፈሩት ዙሪያ የሠፍራል</u> በማለት እግዚአብሔርን በሚፈሩ ሰዎች ዙሪያ የእግዚአብሔር መልአክ የሚገኝ መሆኑን ያስረዳል።
ጌታችን መድኀኒ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል ‹‹ከእነዚህ ከታናናሾቹ አዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘውትር የአባቴን ፊት ያያሉና›› ማቴ 18፡10 እንዳለ ቅዱሳን መላእክት ዘወትር ከእግዚአብሔር ሕዝብ አይለዩም።

3ኛ <u>ያድናቸውማል</u> በማለት የቅዱሳን መላእክትን አዳኝነት ያረጋግጣል አዳኝ በመሆናቸው ላይ እስራኤልን ከፈርኦናውያን ማዳናቸው ዘጸ 14፥19 ። ሠለስቱ ደቂቅንና ዳንኤልን ከእሳትና ከአንበሳ ዳን 3፥25፤ዳን 6፥22። ቅዱስ ጴጥሮስን በእስር ቤት እንደጠበቀውና እንዳዳነው።ሐዋ 12፥11።

Scanned with CamScanner

ያዕቆብም የልጁ የዮሴፍን ልጆች ምናሴንና ኤፍሬምን ሲባርክ «አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ የሄዱለት እርሱ እግዚአብሔር፣ ከታናሽነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እኔን የመገበኝ እግዚአብሔር፣ ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ እርሱ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ» ብሏል (ዘፍ. 48፥6)። በዚህም መላእክት ከክፉ ነገር ሁሉ የሚያድኑና የሚጠብቁ እንደሆኑ፣ መባረክም እንደሚችሉ አስገንዝቧል።

7.1 የቅዱሳን መላእክት አማላጅነት

የቅዱሳን መላእክት አማላጅነት በቅዱስ መጽሐፍ በሰፊው ተገልጦ እናገኘዋለን«...የእግዚአብሔር መልአክ መልሶ አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ እነዚህን ሰባ ዓመት የተቆጣሃቸውን ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከመቼ ነው; አለ...እግዚአብሔር መልሶ ከእኔ ጋር ይነጋገር ለነበረው መልአክ በመልካምና በሚያጽናና ቃል ተናገረው። ስለዚህም ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክ እንዲህ አለኝ። ስበክ። እንዲህም በል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ... ወደ ኢየሩሳለም በምሕረት ተመልሻለሁ» (ዘካ. 1፥12-17)።

ጌታ በዘመነ ስብከቱ የቅዱሳን መላእክትን አማላጅነት በምሳሌ ሲያስረዳ «አንድ ሰው በታወቀች በወይኑ ቦታ ውስጥ በለስ ነበረችው። ፍሬ ሊለቅም ወደ እርስዋ ሄደ አላገኘም። የወይኑን ጠባቂም የዛችን በለስ ፍሬ ልለቅም ስመላለስ እነሆ ሦስት ዓመት ነው። አላገኘሁም። እንግዲህስ ምድራችንን እንዳታቦዝን ቁረጣት አለው። እሱም መልሶ እንዲህ አለው፣ ‹አቤቱ የዘንድሮን እንኳን ተዋት። ዙሪያዋን አፈር እስካስታቅፋት፣ ፍግም እስካፈስሰባት ድረስ። ምናልባት ለከርሞ ታፈራ እንደሆነ፣ ያለዚያ ግን እንቆርጣታለን›።» (ሉቃ. 13፥7-9)።

በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር የተናገረው የበለስዋ ባለቤት እግዚአሔር ነው። በለስ የሰው ልጅ ነው። የወይኑ ጠባቂም ጠባቂ መልአክ ነው። ፈጣሪያችን በሥራችን አዝኖ በሚፈርድበት ጊዜ አማላጆቻችን መላእክት «አቤቱ ጌታ ሆይ ይህቺን ያሁንዋን ብቻ ታገሥ፣ እኛ ተራድተን መልካም ምግባር የማይሠራ ከሆነ እንደፈቃድህ ይሁን» በማለት በአማላጅነታቸው ይራዳሉ። ሙሴ እሥራኤል እግዚአብሔርን አሳዝነው ጽኑ ፍርድ ተፈርዶባቸው ሳለ የፈረደውን ፍርድ በምልጃው እንዲያነሣ እንዳደረገው ሁሉ ማለት ነው (ዘጸ. 32፥10-14)።

Scanned with CamScanner

የቅዱሳን ጸሎት የሚያርገው በመላእክት እጅ ነው፡፡ ለዚሁም ማስረጃ የሚሆነን በዮሐንስ ራእይ ላይ ተጽፎ የምናገኘው ነው፡፡ «...የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው፡፡ የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር በመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ፡፡» (ራእይ 8፥3-5)

7.3 የቅዱሳን መላእክት ጠባቂነት

- በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ ዘጸ 23፥20፣ዕብ 90፥6
- ክፉ ሰዎች (የሰዶምና የገሞራ) ሎጥን በከበቡት ጊዜ መላእክት ጠብቀውታል
- ነቢዩ ኤልሳዕ የነበረበትን የሰማሪያ ከተማና ሳምራውያንን ቅዱሳን መላእክትን ጠብቀዋል ስለ ነቢዩ ኤልሳዕ ቅድስና ፪ ነገ 6፥14፡፡
- ቅዱሳን መላእክት የሰው ልጆችን እንደሚጠብቁ እነሆም አንድ ቅዱስ ጠባቂ ከሰማይ ወረደ በማለት ነቢዩ ዳንኤል ተናግሮአል፡፡ዳን 4፥13፡፡

8. ቅዱሳን መላእክት ስግደትና ክብር ይገባቸዋል

ስግደት የባሕርይና የጸጋ ተብሎ በሁለት ይከፈላል

- ለቅዱሳን የሚቀርበው የጸጋ ስግደት ነው
- ለቅዱሳን መላእክት መስገድ የእግዚአብሔርን ጸጋ ማክበር ነው፡፡ቅዱሳን ሰዎች ለቅዱሳን መላዕክት እንዲሰግዱ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል፡፡

‹‹እሱም ወደ እርሱ ቀርቦ ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህን አለው፡፡ እርሱም አይደለሁም እኔ የእግዚአበሔር ሠራዊት አለቃ ሆኘ አሁን መጥቻለሁ አለ፡፡ ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደና ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ንገድንነው አለው፡፡ ›› 5፥14

‹‹ሁለቱ መላእክትበመሸ ጊዜ ወደ ሰዶም ገቡ ለጥ ሎጥም በሰዶም በር ተቀምጦ ነበር፡፡ ሎጥምባቸው ጊዜ ለቀበላቸው ተነሣ ፊቱንም ደፍቶ ወደ ምድር ሰገደ›› (ዘፍ 19፥1)

‹‹የመልአኩን ድምጽ በሰማሁ ጊዜ ደንግጬ በምድር ላያ በግምባሬ ተደፋሁ ›› ዳን 10፥9

በዮሐንስ ራዕይ የተጻፈው ወንጌላዊው ዮሐንስ ለእግዚአብሔር መልአክ በሰገደ ጊዜ መልአኩ "እንደታደረገው ተጠንቀቅ ከአንተ ጋር የኢየሱስ ስም ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ለእግዚአብሔር ስገድ" ብሎታል፡፡

Scanned with CamScanner

9. መለአኩ ቅዱስ ዮሐንስን ለምን አትስገድልኝ አለው

ቅዱስ ዮሐንስ የሰገደው ለቅዱሳን መላእክት ስግደት እንደሚገባ አውቆና ተረድቶ ነው። መልአኩም አትስገድልኝ ያለው ስለሦስት ነገር ነው።

9.1 ስለትህትና

ዮሐንስ የእግዚአብሔር መልአክ አትስገድልኝ ካለው በኋላም እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ሰግዷል መልአኩም በተመሳሳይ ቃል አትስገድልኝ ብሎታል ራዕ 22፥9፣ምሳ 29፥23 ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ መልአኩ አትስገድልኝ እያለው ደግሞ የሰገደለት ለመላእክት ስገደት እንደሚገባቸው ስለሚያውቅና እንደ ሐዋርያነቱም ለማስተማር ነው እነጅ ተሳስቶ አለምሆኑን የቅዱስ የሐንስን ማንነት ጠንቅቆ ማወቅ በቂ ነው።መልአኩም አትስገድልኝ ማለቱ ስለትህትና ነው እንጅ ስግደት ስለማይገባው አይደለም።‹‹ትዕቢተኞችን ይቃወማል ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል›› እንዲል።ያዕ 4፥6።

9.2 ስለቅዱስ ዮሐንስ ክብር

በሁለተኛም ደረጃ መልኩ አትስገድልኝ ያለው ለዮሐንስ የተሰጠውን ክብርና ቅድስና የነበረውን ንፅሕና ስለሚያውቅ ነው።የቅዱስ ዮሐንስ ክብር ከመልአኩ ክብር ጋር እኩል ሆኖ ስለነበር ይህንን ክብሩን ሊገልጽለት ስለፈለገ እኔም አንተም ለእግዚአብሔር እንስገድ አለው።

9.3 ስለ ሥልጣነ ክህነት ክብር ሲል ነው

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ የካህናትን ክብር ሲናገር ‹‹ካህናት ሰውን ሁሉ እንደሚዳኙ አታውቁምን እናንተሰውን ሁሉ የምትዳኙ ከሆናችሁ ይህን የትንሹን ነገር ልትፈርዱ አይገባችሁምን።የዚህን ዓለም ዳኝነት ተውትና መላእክትን ስንኳ እንድንገዛ አታውቁምን›› 1ኛ ቆሮ 6፡2-3 ይላል። መልአኩም ስለ ሥልጣነ ክህነት ክብር ሲል አትስድልኝ ብሎታል እንጂ ስግደት ስለማይገባው እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል።

Scanned with CamScanner

10. ድርሳነ ቅዱስ ገብርኤል ዘሐምሌ

እለ እስክንድሮስ የተባለ መኰንን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑትን ክርስቲያኖች ለመቀጣትና ሌሎችም ፈርተው ክርስትናን እንዳይፈልጉት ለማድረግ አስበ ስም፣ ጨው፣ ባሩድ፣ ሙጫ፣ የዶሮ ማር፣ እርሳስ፣ ብረት፣ ቅንጭብ፣ ቁልቁል አንድ ላይ ተቀላቅሎ በብረት ጋን እንዲፈላ አዝዞ ነበር። ጭፍሮቹም እለእስክንድሮስ እንዳዘዛቸው ከአደረጉ በኋላ ያዘዘኸንን ሁሉ ፈጸምን እሳቱ ነዶ ፈልቷል፣ ድምፁ እንደነጎድጓድ ይሰማል፣ ወላፈኑም እንደ ፀሐይ ነፀብራቅ በፊት ይጋረፋል፣ የፍላቱም ኀይል አርባ ዐራት ክንድ ያህል ከፍታ ወደላይ ይዘላል፣ እንግዲህ በውስጡ የሚጣሉትን እዘዝ አሉት።

በዚህ ጊዜ ሕፃን ቂርቆስና እናቱ ኢየሉጣ በክርስቶስ ስም ስለሚያምኑ አሥረዋቸው ነበርና ከፍላቱ ሊጨምሯቸው ከእሥር ቤት አወጧቸው። ሲወስዷቸው ፍላቱ ወደ ላይ በሚዘል ብረት ጋን ውስጥ ለመጨመር የእነዚህን ቅዱሳን እሚሚት ያዩ ዘንድ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች እንዲሰበሰቡ ታዘዘ። በዚህ ጊዜ ቅድስት ኢየሉጣ የፍላቱን ጩኸት በሰማችና ባየች ጊዜ ተሸበረች፣ ተዘጋጅቶላት ከነበረውም ክብር ልታፈገፍግ ሞከረች።

ልጅዋ ቅዱስ ቂርቆስ ግን "እናት ሆይ ከዚህ የብረት ጋን ግርማ የተነሣ አትፍሪ፣ ድንጋፄም አይደርብሽ፣ አናንያንና አዛርያን፣ ሚሳኤልንም እግዚአብሔር ከዕቶኑ እሳት እንዳወጣቸው ሁሉ እኛንም ከዚህ ከብረት ጋን ሊያወጣን ችሎታ ያለው መሆኑን አትጠራጠሪ።" "እናት ሆይ ከዚህ ከሚያልፈው ዓለም ጭንቅና መከራ ለማዳን ስትይ በማያልፈው በዘለዓለም እሳት ለመቀጣት ትመርጫለሽን? ይህስ አይሆንም፣ ይቅርብሽ፣ በአሁኑ ጊዜ እግዚአብሔር በመካከላችን አለና ይረዳናል።" "እናቴ ሆይ ሶስናን ከአደ ረበናት፣ /መምህራነ አይሁድ/ ዳንኤልን ከአፈ አናብስት ያዳነ እሱ እኛንም ከዚህ የጋን ፍላት ያወጣናል። ይልቁንም እግዚአብሔር በዚህ የብረት ጋን ውስጥ ግዳጃችንን ልንፈጽም ፈቅዶ ከሆነ ኢዮብ ንብረቱንና ገንዘቡን፣ ልጆቹንና ሚስቱን፣ በመጨረሻም የተፈጥሮ አካሉን ባጣ ጊዜ እግዚአብሔርን አመስግነዋለሁ፣ እግዚአብሔር ሰጠ፣ እግዚአብሔር ነሣ፣ /ወሰደ/ እግዚአብሔርም እንደ ወደደ አደረገ፣ ከማለት በስተቀር ምንም የተናገረው ክፉ ነገር እንደሌለ ሁሉ እኛም የሱን ዓላማ በመከተል ይህን መከራ ልንታገሥ ይገባናል" አላት። ነገር ግን እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ

በዚህ ምክር ልትጽናና ባለመቻሏ ቅዱስ ቂርቆስ ዓይኑን ወደ ሰማይ አቅንቶ ቅዱሳኖቹንም ድል ነሣኒቸው፤ ብሎ እንዳይመካ ከመንጋውም አንድ በግ ቀማሁ፤ በ"አቤቱ አምላኬ ሆይ ይህችን ነባሪያህን ከርስትህ የምትለያት ከሆነ ከባለሚልነትህ መጽሐፍ ፋቀኝ፤ አቤቱ አዝመራውን አቃጥለህ ፍሬውን ልትባርክ ትወዳለህን ይህን እንዳታደርግ ግን ቸርነትህ ትከለክልሃለች፡፡ አቤቱ እንጨቱን ቆርጣችሁ አንድዱት፤ ቅጠሉን አንድዱት፤ ቅጠሉን ግን ጠብቁት፤ ብለህ ልታዝ መለኮታዊ ባሕርይህ አይደለም፤ ነገር ግን እንጨቱንም ቅጠሉንም ባንድ ጠብቁት፤ ብለህ ታዝዛለህ እንጂ፤

እንግዲህ በዚህ ምክንያት ይህን ያየ ሁሉ ማዳን የሚችል አምላክ ቢኖራቸውስ ኖሮ ከዚህ ከእሳት ባልሸሹም ነበር ብሎ አይጠራጠር፡፡ አቤቱ ዲያብሎስም ከባለሥልጣኑ ይልቅ እኔ በረታሁ፤ በማለት እንዳይደነፋ ለናቴ ጽኑ የሆነ ኃይለ መንፈስ ቅዱስን ስጣት" ብሎ በጸለየ ጊዜ ዲያብሎስ ከኢየሉጣ አጠገብ ብን ብሎ ጠፋ፡፡

ከዚህ በኋላ ቅድስት እናቱ በሰማያዊ መንግሥት አባት የሆንከኝ ልጄ ሆይ ጌታህ ኃይልን ሰጥቶኛልና የሚጠብቀንን ገድላችንን ፈጽመን ድል እናድርግ፤ እነሆ በብረት ጋኑ ውስጥ የሚነደውን እሳት በማይበት ጊዜ በለምለም /በምንጭ/ ላይ እንደሚወርድ ጠል ሆኖ አይቼዋለሁና አለችው፡፡ እኒህም ቅዱሳን ይህን በሚነጋገሩበት ጊዜ በውስጡ አንገትን የሚቆለምም፣ ልብን የሚያቀልጥ፣ ሆድን የሚሠነጥቅ፣ ሥርን የሚበጣጥስ መሣሪያ ካለበት የብረት ጋን ውስጥ ጨመሯቸው፡፡ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል ከሰማይ ወረደና የብረቱን ጋን እሳት አጠፋው፤ ከቅዱሳኑም አንዳቸውንም ሳያቃጥላቸው የብረቱ ጋን ማቃጠሉና መፍላቱም ፀጥ አለ፡፡

ወንድሞቻችን ሆይ እንግዲህ በጭንቃቸው ጊዜ ገድላቸውን እስኪፈጽሙ ድረስ ይህ መልአክ ከሰማዕታትና ከጻድቃን ጎን እንደማይለይ እወቁ፡፡

ለኃጥአንም ኃጢአታቸውን ይቅር ይላቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ይጸልይላቸዋል። እኛም የዚህን የሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል በዓሉን በየወሩ እያከበርን አማላጅና ወዳጅ እናድርገው፤ በዚህም በሚመጣውም ዓለም ሊረዳን ይችላልና። ዳግመኛም አለ እስክንድሮስ ሀሳቡ ሳይሳካለት ስለቀረ ዐሥራ አራት የሾሉና የጋሉ የብረት ችንካሮች አምጥተው ሰባቱን በእናቱ በኢየሉጣ አካል፣ ሰባቱን በቂርቆስ አካል ይቸነክሯቸው ዘንድ ጭፍሮቹን አዘዘ። ዳግመኛም የሕፃኑን የአራስ ቆዳ ገፈው እሳት ውስጥ ይጨምሩት ዘንድ አዘዘ። አሁንም መልአኩ መጥቶ ይህን መከራ አራቀለት። ቀጥሎም በመቃን ውስጥ ጨምረው በገመድ እንዲጎትቱት አዘዘ፤ በዚህም ጊዜ መልአኩ አዳነው። ሕዝቡም ይህን ሁሉ ተአምር በአዩ ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገኑት፤ ቅዱስ ገብርኤልንም አከበሩት።

11. ማጠቃለያ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስለ መላእክት ተራዳኢነት ጠባቂነት አዳኝነት እና አማላጅነት ስታስተምር የማይዋጥላቸው ተሐድሶዎች እና መናፍቃን እንዴት ሊሆን ይችላል በማለት በዙ ጊዜ ግራ ሲጋቡ ይታያል:: ስለዚህ ወገኖች እና የምዕራባወያን ባህል ተፅእኖ ላደረባቸው ሁሉ በቅርብ ጊዜ የዜና አወታሮችን ስላገኘና በብዙ ሰዎች ዘንድም መነጋገሪያ ነበረውን ታሪክ ማስታወስ ተገቢ ስለሆነ እንደሚቀጥለው ይቀርባል::

የመላእክት መገለጥና ተራዳኢነት የፕሮቴስታንት ፓስተር የሆኑት ዶ/ር ወዳጄነህ መሐረነ የመላእክት አለቆች በእናት ሀገር በሚለው መጽሐፋቸው ላይ የጻፉትን ማጠቃለያ እናደርገዋለን::

ጊዜው በሩሲያ ኮሚኒዝም የሚሰበክበት፤ እግዚአብሔር እንደሌለም ማሳመኛ የሚደሰኮርበት፤ሃይማኖት የኢምፔርያሊስቶች መሣሪያ ነው ተብሎ የሚታመንበት ጊዜ ነበር:: ኦሌንግ አትጎብ፤ብላድሚር ሶልብየብና ሊኒድ ኪዝም የሚባሉ የሩሲያ የጠፈር ሳይንስ ተመራማሪዎች ነበሩ:: ይህንኑ እምነት እነዚህ ሦስቱ ታዋቂ ሳይንቲስቶችም ተጋርተዋል:: ታዲያ እነዚህ ተመራማሪዎች ወደ ጠፈር ሄደው የተላኩበትን ተልእኮ በትጋት እየተወጡ ሳለ በሄዱ 155ኛው ቀን አንድ አስደንጋጭ ክስተት ገጠማቸው:: በድንገት መንኮራኩራቸው በብርቱካናማ ብርሃን ተሞላች የብርሃኑ ብርታትም እጅግ ከፍተኛ ስለነበር ሳይንቲስቶቹ ለጥቂት ደቂቃዎች አጥርተው ማየት ተሳናቸው::‹‹የእሳት አደጋ ተነስቷል ወይም የመንኮራኩሯ አንድ አካል ፈንድቷል›› ብለው ገመቱ........እጅግም ተደናገጡ!

ከጥቂት ሰኮንዶች በኋላ ሦስቱም ሳይንቲስቶች ወደ ውጭ ሲመለከቱ ግን አይናቸውን ማመን አልቻሉም:: እንዲህ ያለ ነገር ይገጥመናል ብለው በህልማቸውም በእውናቸውም አስበው አያውቁም ነበር:: ገር ግን አይኖቻቸው ድንቅ ነገር አዩ!! .... ሰባት ትላልቅ ውብ መላእክት መንኮራኩሩን ከበውት ነበር:: መላእክቱ እጅግ ትላልቅ መሆናቸው የሚያስፈራ ይሁን እንጂ የሚያማምር የሰው ፊትና ቁመና ነበራቸው:: በደማቅ ብርሃን የተሞሉ አካላት ሆነው የሚበሩባቸው ክንፎችም አሉአቸው:: ተመራማሪዎቹ ፈዘው ቆመው እያዩ ሰባቱ መላእክት በግልፅ መንኮራኩሩን እየከበቡ ይንሳፈፉ ....ይበሩም ነበር::

Scanned with CamScanner

ሳይንቲስቶቹ ያዩትን ነገር በታላቅ መደነቅ ሆነው በምድር ላለው የመቆጣጠሪያ ጣቢያ ሪፖርት አደረጉ፡፡ በጣቢያው የነበሩ ሠራተኞች ግን ‹‹ከድካም የተነሳ መቃዠት ጀምረዋል›› በለው ተዘባበቱባቸው እንጂ ያመናቸው አልነበረም፡፡

ከጠቂት ቀናት በኂላ ሦስት ተጨማሪ ተመራማሪዎች በሌላ መንኮራኩር ወደ ጠፈር ተልከው የቀደሙትን ተቀላቀሉአቸው እነሱም በደረሱ በሰዓታት ውስጥ እግዚአብሔር እንግዶቹን ሳይንቲስቶች ሊያሳምናቸው የፈለገ ይመስል ያች መንኮራኩር እንደገና በታላቅ ብርቱካናማ ብርሃን ተሞላች፡፡ አሁን በቁጥር ስድስት የሆኑት ጠፈረተኞች በአንደነት ወደ ውጭ ተመለከቱ.....ሁሉም በመደነቅ ፈዘው ቀሩ!.....ከውጭ ያዩት ሰባት ትላልቅ መላእክትን ነበር! መላእክቱ እንደቀደመው ሁሉ የሰው መልክና ቁመና ሲኖራቸው የሚበሩበትም ክንፍ ነበራቸው፡፡ በመጠናቸውም እያንዳንዳቸው ትላልቅ የመንገደኛ አውሮፕላን ያካክሉ ነበር፡፡ መላእክቱ እየበረሩ መንኮራኩሩን ይጠብቃሉ፡፡ፈገግ ብለው አዩአቸው .....መላእክቱ .....ተመራማሪዎቹን! ስድስቱም ሳይንቲስቶች ፈዘው ቆመው ይህንን ልዩ ትእይንት እየተመለከቱ ነበር፡፡ ከዚያም መላእክቱ በድንገት ከአይናቸው ተሰወሩ፡፡ ይህንን የተመራማሪዎቹን ገጠመኝ ‹‹ዋሸንግተን ፖስት›› እና ‹‹ ፖስተን ፖስት››የተባሉ ጋዜጦች በጊዜው ዘግበውታል፡፡‹‹ በእግዚአብሔር የማያምኑ ጠፈረተኞች ሰባት መላእክትን አዩ›› የሚል ዘገባ ወጣ! ይህም በዓለም ዙሪያ መነጋገሪያ ጉዳይ ሆኖ ሰነበተ!

ይህንንኑ አስደናቂ ነገር የቅዱሳን መላእክትን ተራዳኢነትና አማላጅነት አንቀበልም ከሚሉት ወገን የነበሩትና የፕሮቴስታንት ፓስተር የሆኑት ዶ/ር ወዳጄነህ መሐረነ የመላእክት አለቆች በእናት ሀገር በሚለው መጽሐፋቸወው ላይ በማንሳት ሲደነቁ ይታያሉ፡፡ ታዲያ በዚህ ዘመን ስለቅዱሳን መላእክት የተጻፈውን ከቅዱሳት መጻሕፍት እየተጠቀሰ ሲነገረው የፈረንጅ ጋዜጠኛና የፕሮቴስታንት ፓስተር ካልነገረን አናምንም ለሚሉ ተሐድሶዎችና መናፍቃን ቸርነቱ የማያልቅበት እግዚአብሔር በዚህ መንገድ እንዲማሩ እድል ሰጥቶአቸዋልና በማስተዋል ቦመለከቱት መልካም ነው፡፡

Scanned with CamScanner

የእግዚአብሔር ቸርነት
የድንግል ማርያም አማላጅነት
የቅዱሳን መላእክት ተራዳይነት አይለየን!!!

Scanned with CamScanner